# ይድረስ ለትግራውያን ወንድሞቼና እህቶቼ

ካንዱ ኢትዮጵያዊ ወንድማችሁ

መጋቢት 17 የዶ/ር አብይ አህመድ የኢህአደግ ሊቀመንበር ቀጥሎም መጋቢት 23 ያገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው መመረጥ ለአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ የተስፋ ጮራ እንደጣለ ሊካድ አይችልም። ባንጻሩም በተለያዩ የብዙሃን መገናኛዎች እንደሚሰማው ይህ ለውጥ ብዙ ሊባሉ የሚችሉን ትግራውያኖችን ስጋት ውስጥ ከቷቸዋል። ይህንንም ጽሁፍ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ይህ ለውጥ ለትግራውያን ወንድሞቼና እህቶቼ እንደሌላው የኢትዮጵያ ዜጎች ትልቅ እድል እንደሆነ ያለኝን እምነት ለማጋራትና ከሌላው ህዝብ ጋር መሰለፍ እንዳለባቸው ለማሳመን ነው። እንዲያውም በኋላ እንደማስረዳው ለህወሓትና በህወሓት እርዳታ የሀገሪቷን ኢኮኖሚንና የመንግስት ተቋማት ለተቆጣጣተሩትም ጥቂት ትግራውያን ጭምር ትልቅ እድል ነውና እነርሱም የለውጡን እርምጃ ሳይረፍድ እንዲቀላቀሉ ለመማጸን ነው። ጽሁፉንም ቀጥተኛና እውነት ተኮር ለማድረግ ስለፈለኩኝ ጽሁፉ ውስጥ ያሉ አንዳንድ የሚዋጉ እውነታዎች የተወሰኑ አንባቢያንን ሊያስደነግጡ ይችላሉ። ይህንንም የማደርገው እነርሱን ለማስበርገግ ሳይሆን እውነቱ ሳይፈርጥ የኢትዮጵያ ችግር አይፈታም ብዬ ስለማምን ነው።

ሰው ሆኖ የማይሳሳት የለም። ህብረተሰብም የሰዎች ስብስብ እንደመሆኑ ይሳሳታል። ብዙም ግዜ ለህብረተሰብ ስህተት የተወሰኑ ልሂቃኖችና መሪዎች አስትዋጾ ከፍተኛ ነው። ልምሳሌ በግዜው የሰለጠነና የተማረው የጀርመን ህዝብ ሂትለርን በመሰለ እዕኩይ ሰው ተታሎ ሁለተኛ አለም ጦርነት ውስጥ ገባ።

ተራው ሰው የተወሰኑ ልሂቃኖችና መሪዎች አምኖ ከተከተላቸው በኋላ እስረኛቸው (hostage) ይሆናል። ምክንያቱም በያጋጣሚው የችግሩ ተባባሪ እንደሆነና የፍርድ ቀን ቢመጣ "ጉዱ እንደሆነ"፥ ያለው ምርጫም እነርሱን መከተል ብቻ እንደሆነ መሪዎቹ ስለሚነግሩት ነው።

የትግራይም አጣብቂኝ ይህ ይመስለኛል። የህወሓት መሪዎችና ግብራበሮቻቸው እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የኢትዮጵያ ህዝብን እየበዘበዙ ለማበልጸግ ሲሉ የዋሁን የትግራይ ህዝብን አሳሳቱ። ለዚህም ዕኩይ ዓላማቸው የሌላው ኢትዮጵያ ዜጎችን ሲያሰቃዩ የትግራይ ተራውን ህዝብ ቢቻል እንዲተባበርና የድርጊቱ ተካፋይ እንዲሆን፥ ካልሆነም ጸጥ ብሎ እንዲያይ አሳምነው ባራዳ ቋንቃ እንደሚባለው "ማኖ" አስነኩት።

ይህንን ስል ግን የህወሓት መሪዎችና ታጋዮች ከመጀመሪያው ዕኩይ ዓላማ ይዘው ነው የተነሱት ማለት አይደለም። እንዲያውም እብዛኛዎቹ ቢያንስ፤ በነርሱ አተስተሳሰብ፤ ለትልቅ ዓላማ ነው የተዋጉት ብዬ አምናለሁ። ስለተዋጉና ስለሞቱ ግን የዛን ግዜ ዓላማቸው ትክክል ነው ማለት አይደለም። ቢሆን እንኳን ዓላማቸውን በመንገድ አይለወጡም ማለት አይደለም። ባይለውጡም እንኳን ስልጣንን መቆጣጠር መብት ልንሰጣቸው በምምንም አይገባም። የተዋጋና የሞተ ቡድን ስልጣን መቆጣጠር መብቱ ነው ከተባለማ ኢህአፓን፥ ደርግን፥ ኦነግን፥ አብነግን፥ ግንቦት 7 ና ሌሎቹንም አፈላልገን ስልጣኑን ማካፈል ይኖርብናል። ስልጣን የሚገባው የኢትዮጵያ ህዝብ በነጻ ምርጫ ለዛሬ ችግሬ ፈቺ አንተ ነህ ያለው ብቻ ነው። ሌላውን መስፈርት ለበለጠ ችግር ይከተናልና ከጭንቅላታችን ማውጣት አለብን። የጦርነት ጀግኖቻችንን የምንናመሰግነው ስልጣንን በመስጠት መሆን በፍጹም የለበትም።

ትግራዊያን በህወሓት ተታለዋል ሲባል ግን እንድም ትግራዊ ይህንን እኩይ ተግባር አልተቃወመም ማለት አይደለም። ገና ከመጀምሪያው ይህንን ተቃውመው ለስደት፥ ለሞትና ለእንግልት የተዳረጉ እንዳሉ እናውቃለን። ለግዜው ግን እድሜ ለህወሓት እነዚህ ክቡር ሰዎች በብዙ ትግራዊያን እንደከሃዲ እንዲታዩ አድርጓቸዋል። ምክንያቱም የህወሓት ስትራቴጂ ዋና ምሰሶ የሆነውን "የትግራይ ህዝብን ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ መለያየት" ታክቲክ

ይንዱብታልና። ለዚህም ነው እነዚህን ተቃዋሚዎች ከሌላውም ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ በላይ የሚጨክንባቸው። ቀኑ ሲደርስ ግን ልክ በደቡብ አፍሪካ ለጥቁር ህዝቦች የታገሉት ነጭ ፖለቲከኛዋ እንደ ሔለን ሱዝማን ፥ ወይንም በናዚ ጀርመን ይሁዳውያንን እንዳዳኑ የጀርምን ናዚ እባል እንደ ኦስካር ሺንድለር ስማቸው ከተቀበረበት ይወጣል።

ሰዎችና ህብረተሰቦች የሰሩት ስህተቶች አንዳንዶቹ ትንሽ ሲሆኑ የሰዎች ግንኙነቶች ውስጥ ከፍተኛ ችግር ባያስከትሉም ሌሎቹ ደግሞ የከፉ ችግሮች ያመጣሉ፤ እንዲያውም የችግሮች አዙሪት ውስጥ ይከታሉ። እድለኛና እስተዋይ ሰው ወይም ህብረተሰብም ስህተቱን አምኖ ሌላ የከፋ ችግር (ሌላውም ላይ እራሱም ላይ) ሳያመጣ ከጎዳው ሰው ወይንም ህብረተሰብ ጋር ታርቆ ወደ ቀዳሚው ጥሩ ግንኙንቱ ይመለሳል። ጠባሳ ይኖራል፥ ቅጣትም የሚያገኙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ ግን ሊከተል ከነበረው ችግር ሲነጻጸር ኢምንት ነው።

ታሪክም ይህንን ያሳየናል።

ደቡብ አፍሪካ በአፓርታይድ ዘመናት የነጮች የበላይነትን የሚያረጋግጥ ስርዓት ያሰፈኑ መንግስታቶች ነጩን ህዝብ ባብዛኛው በጥቅም በመደለል የወንጀሉ ተባባሪ እንዲሆን አድርገውታል (በተሳታፊነት ወይንም ዝም በማለት) ። ይህም የዓድሎ ስርዓት ዘላለማዊ ሊሆን አልቻለም። ብዙ ደም ፈሶም ቢሆን የስርዓቱ መሪዎች ስህተታቸውን እምነው አፓርታይድን አፍርሰዋል። አፓርታይድም ሊገረሰስና የሁሉም ዜጋ መብት የተከበረበት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሊቋቋም ችሏል። የአፓርታይድ መሪዎች ህዝቡን ለዘመናት ሲያስፈራሩት እንደነበረው አገሪቷ ለነጮቹ የማትመች እልሆነችም። ዛሬ ሁሉም ያገሪቱ ዜጎች (ነጮቹም ጭምር) ያለጦርነት ስጋት ይኖራሉ። ያሉትም ሌሎች ችግሮች በመሆኑ ከአፓርታይድ የተወረሱ፥ ባብዛኛው ከጥቁሮቹ ድህነት ጋር የተያያዙ ናቸው። አብዛኛዎቹ ነጮችም ከነበሩበት አጣብቂኝ ያወጧቸውን ኔልሰን ማንዴላን እንደ ነፍስ አዳኝ የሚያዩዋችው ለዚህ ነው።

በናዚ ጀርመን፥በፋሽስት ኢጣሊያ፥በዩጎስቪያ የሆነውም ተመሳሳይ ነው። መሪዎች የብሄር የበላይነትን በመስበክ ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ የአገራቸው ህዝብን ለጦርነትና ለድህነት ዳርገው መጨረሻቸውም አላማረም።

ውድ ትግራዊው እንባቢዬ። ይህንን ስታነብ እንዴት ህወሓትን ከነዚህ እኩይ አገዛዞች ጋር ያመሳስላቸዋል ትል ይሆናል። እውነቱ ግን የመጠን ጉዳይ ይሆናል እንጂ የነርሱን ጥፋቶች ህወሓትም አጥፍቷል። ጥላቻን ሰብኳል። የትግራይን ህዝብ ወደተሳሳተና መውጫ ወደሌለው መንግድ መርቷል። የሌላውን ብሄሮችን ሃብት ዘርፏል። ለ27 ዓምትታት የሃገሪቷን ቁልፍ ስልስጣኖች በብቸኝነት ይዟል።

እኔ ይህንን ስል ከህወሓትና ከደጋፊዎቹ የምትሰማው ግን "ይህ ሁሉ ስም ማጥፋት ነው" ነው። ሃቁን የሚያወጣው ታሪክ ወይንም ከታደልን፥ ገለልተኛ ፍርድ ቤት ነው። ለግዜው ግን አንዲት ነገር ብቻ ባስቸግርህ ሊያቀራርበን ይችላል። እባክህን አንድ የምታምነው ትግራዊ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ጓደኛህን ይህንን የኔንና የብዙ ዜጋ እምነት ያምን እንደሆነ ጠይቀው። መልሱ እዎን እንደሚሆን በሙሉ ልቤ እናገራለሁ። ምናልባት የሚያስቸግርህ ትግራዊ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ጓደኛ ማግኘት ይሆናል። እድሜ ለህወሓት ነጣጥሎናልና!

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚያምነው ሁሉም ነገር ግን ሃቅ ላይሆን ይችላል ትለኝ ይሆናል። በዚህ ካንተ ጋር እስማማለሁ። ሆኖም ሌባ ወይንም ነፍሰ ገዳይ ልጅ ያላት እናት የልጇን ሌብነት ወይንም ገዳይነት የምታምነው ከሁሉም መጨረሻ እንደሆነ እንስማማለን። ባይኗ የምታየውን እንኳን ትክዳለች። ትግራዊውያንም ሀቁን ማመን ይከብዳቸዋል ብዬ አምናለሁ፥ ምክንያቱም ወንጀሉን የሰሩት ወንድምና እህቶቻቸው ወይንም ልጆቻቸው ናቸውና። ግን ሀቅ ላይ ተመስርተን

ካልሆነ ወደፊት ማለት የማይቻልበት ግዜ እየመጣ ስለሆነ ሀቁን ሁላችንም ብናፈላልግ የተሻለ ነገን ለመፍጠር እድል እንፈጥራለን።

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፤ለውጡን በሙሉ ልብ ተቀላቀሉ። የህወሓት ስርአት ሰለባዎች እናንተም ናቹህና። ሳትጠይቁት የበላይ ናችሁ ብሎ ነገደባችሁ፤ ሳትጠይቁት ከወንጀሉ አነካክቷችሁ አጣብቂኝ ውስጥ ከተታችሁ። ለ27 ዓምትታት ህወሓት ደህንነቱን፣ የጦር ሃይሉን፣ ፍትህ ተቋማትን፣ኢኮኖሚውን ስለያዝኩኝ አይዟችሁ፣ግደሉ፣ዝረፉ፣የስራ እድሉን፣ የትምህርት እድሉን ለዘመዶቻችሁ አከፋፍሉ፣ አላችሁ። ምርጫ 97 ላይ የህወሓት የበላይነት ሊያበቃ እንደሚችል ጠቋሚ ነበር። ነገር ግን እድሉን እናንተም ህወሓትም አልተቀማችሁበትም። ይህ ነገር አያዋጣም እንደማለት በተቃራኒው ህወሓት አጋጣሚውን ለለደጋፊዎቹ ሃይሉን ማሳያ አደረገው። የምርጫ ስርዓቱን፣ደህንነቱን፣ የጦር ሃይሉን፣ እንደሚቆጣጠር፣ ምንም እደማያሰጋቸውና ከበፊቱም በባሰ ሌላውን ኢትዮጵያዊ የሚያስቆጣ ተግባር እንዲሰሩ የገፋፋበት አጋጣሚ ነበር። ለዚህም ምርጫ 97ን ለጥቆ የተመዘበሩት የአዲስ አበባ መሬቶች ምስክር ናቸው።

አሁንም የዶ/ር አብይ አህመድ መመረጥ ያበሰረውን አዝጋሚ ለውጥን (reform) የሚቃወሙና እንዲያውም መፈንቅለ መንግስት የሚመስሉ ሃሳቦችን በትግራውያን ድረ ገጾች ላይ እናያለን። የ97 እይነቱ የምርጫን ውጤት በሃይል የመቀልብስ ሁኔታ ቢመጣ የሚደሰቱ እንዳሉም እንሰማለን። ሁሉም በሚባል ደረጃ መገናኛ ብዙሃን ላይ የሚቀርቡ ትግራውያኖች ሌላውን ኢትዮጵያዊ ያስቆጣውን አስቸኳይ ግዜ አዋጁ ሲደግፉ ይሰማልሉ። ሆኖም ወደድሮው የመመለስ እድል በጣም የተመናመነ ይመስለኛል። ከዚህም በበለጠ ለግዜውም እንኳን ብንመለስ ደግሞ ለማትቀረዋ የኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ለምትኖረው የፍርድ ቀን ለትግራውያን ትልቅ ዕዳ ከመሆን ሌላ ፋይዳ እይኖረውም። ፍትህ ቢረፍድም ትመጣለችና። በኛ ህይወት ግዜ እንኳን ባትደርስ በልጆቻችን ግዜ ትመጣለች። ለልጆቻችን ደግሞ ያልተወራረደ ሂሳብ ባናወርሳቸው ይሻላል ብዬ እምናለሁ።

በኔ እምነት ለህወሓትም ሆነ ለህወሓት ደጋፊዎች ለማይቀረው ስልጣንን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለተመረጠ መንግስት ማስረከብ ከዚህ የተሻለ ግዜ አይኖርም። ምክንያቱም እሁን ሽግግሩ እራሳቸው የፈጠሩት ህገመንግስት ባለበት ሁኔታ፣ ትንሽ ንፋስ ሰሞኑን ቢገባበትም ተባባሪያቸው ድርጅት (ኦህዴድ) የበላይነቱን በያዘበት ሁኔታ ነው። የሚቀጥለው እጋጣሚ ከዚህ ብዙ የከፋ እንደሚሆን ከልብ ይሰማኛል። ለውጡ የሚመጣው በ1966 አይነት እብዮት ወይንም በ1983 አይነት የጦርነት ሽንፈት ይሆናል። እንደምታውቁትም በነዚህ ለውጦች አሸናፊው ለተሸናፊዎቹ ምንም ርህራሄ እላሳየም።

ለኢትዮጵያ ህዝብም እንዳሁኑ አይነት ዘገምተኛ ለውጥ ይበጀዋል ብዬ አምናለሁ። ከላይ እንደጻፍኩት የ1966 ና የ 1983 ለውጦች ለተሸናፊዮቹ ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹም ከደሙ ንጹህ ለሆኑ ዜጎች ብዙ ሰቆቃን አምጥቷል። ረጋ ያለ ለውጥ ደርግ እና ኢህአደግ ሲያሸንፉ የተደረጉትን ዓይነት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሊያስቀር ይችላል። ጠ/ሚኒስትር አብይ እንዳሉትም በንግግርና በመግባባት የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ልንገነባ እንችላለን።

ሌላው መነሳት ያለበት የትግራውያን ስጋት፣ ዴሞክራሲ ቢመጣ እናሳ ብሄረሰብ በመሆናችን በብዙሃኑ እንጨቆናለን የሚል ስጋት ነው። በታሪክም በተለያዩ ግዜአት እናሳ ሆነው የሌላው የበላይ ለመሆን የሞከሩ ብሄሮች መነሻ ይሄው ነው። ባለፈው ክፍለ ዘመን አንዳንድ ማይኖሪቲ ብሄሮች፣ ዴሞክራሲ “ሊያመጣባቸው” የሚችለውን “መበለጥ” ሲፈሩ ምርጫው ውስጥ ብዙሃኑ እንዳይሳተፍ በማድረግ (እንደ አፓርታይድ ደቡብ አፍሪካና ቅድመ እኤአ 1980 ዚምባብዌ) ወይንም ምርጫውን በማጭበርበር (እንደ ቡሩንዲ እስከ 2000 ድረስ እና እንደ ሶሪያ እስከዛሬ ድረስ) ስልጣን ላይ ሊቆዩ ይሞክራሉ። ስልጣኑን ለመቆጣጠርና እኩልነት ብቻ ሳይሆን የበላይነት ያላቸውን ስርአት ለማስፈን ሞክረዋል። ሆኖም ይህን አይነት ስርዓት በ20ኛውና 21ኛው ክፍለ ዘመን ዘላቂነትት እንደሌለው ሁሉም አይተውት ዴሞክራሲን መቀበል ግድ ሆኖባቸዋል።

ዴሞክራሲ ማለት ደግሞ የብዙሃን ጨቋኝነት መሆን የለበትም። ወደዴሞክራሲ የተኬደበት ጉዞ ጥሩ ከሆነ ማይኖሪቲው መብቱ የተከበረበት ሊሆን ይችላል። ደቡብ አፍሪካ የሆነው ይህ ነው። ዛሬ ነጮች ይመርጣሉ፥ ኢኮኖሚው ውስጥም ሆነ አስተዳደር ውስጥ ከፈተኛ ቦታ አላቸው። እንደዛ የጥቁርና የነጭ ግንኙነት ተበላሽቶ የነበረበት አገር እንደአሁኗ አይነት የሁሉም የሆነች አገር መገንባት ከተቻለ፥ እኛ ኢትዮጵያውያን ለክፍለዘመናት የተዋደድን፥የተጋባን፥የተዋለድን፥አብረን ለአንዲት አገር የተዋጋንና የሞትን፥ 27 ዓምቱን ረስተን በትንሹ ልንታረቅ የምንችልበት ምንም ምክንያት የለም። የምንገነባትም አዲስ ሃገር የበቀልና "አሁን ደግሞ የኔ ተራ" የሚባልባት ሳትሆን እውነተኛ ዴሞክራሲ የሰፈረባት፥ ማንኛውም ዜጋ የሚከበርባት ሃገር የማሆንበት ምክንያት የለም።

ለዚህ ግን ከሁላችንም የሚጠበቅ ብዙ ነገር አለ። ትግራውያኖች እራሳቸውን ከህወሓት አላቀው ከሌላው ህዝብ ጋር አዲሲቷን ኢትዮጵያ መገንባት አለባቸው። የህወሓት ጉዞ እዚህ ላይ እንዳበቃ ተገንዝበው፥ ምንም ውለታ እንደሌለባቸው አምነው፥ እራሳቸውን ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ማቀራኘት አለባቸው። ህወሓት በሌላው ህዝብ ላይ ያደረሰው በደል ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ከርሱ ሳይነጣጠሉ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር ለመቀራረብ የሚያደርጉትን ጥረት ከባድ ያደርግባቸዋል። ለህወሓት አይጨነቁ፥ ስራው ወይ ያወጣዋል ወይ ይፋረደዋል።

ሌላውም ኢትዮጵያዊም ሆደ ሰፊ ሆኖ እያንዳዱን ጥፋት አንስቶ የትግራይን ህዝብ ለምሬት መጋበዝ የለበትም። እንደ ወንድማማቾች ጥል ተነጋግሮ፥ተማምኖ፥ይቅርታ ተጠያይቆ፤ምህረትን አውርዶ ፍቅርን ማስፈን አለበት። ለዚህም ግዜው አላለፈም ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም 27 ዓምታቱ ፍቅሩን ሙሉ በሙሉ አልፋቁትም።

እንዲሁም ሌላው ኢትዮጵያዊ ለትግራይን ህዝብ ዘብ መቆም ይጠበቅበታል። በህወሓት ሲጨቆን እንደታገለው ሁሉ የትግራይንም ህዝብ ሊጨቁን የሚፈልግ ማንኛውንም መንግስት ከትግራይ ህዝብ ጋር ሆኖ መታግል እለብት።

ህወሓት አንደገና ቢንሰራራ የቀረው በትግራይ ህዝብና የቀረው ኢትዮጵያዊ መሃል ያለው ፍቅር እየቀነሰ እንዲያውም እየጠፋ ሊሄድ ይችላል። የማትቀረው ቀን ስትመጣና ህወሓት ሲወርድ ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ለትግራውያን ያለው እምነትና ፍቅር ተመናምኖ ወደብቀላ ሊያመራ ይችላል ብዬ እሰጋለሁ። ባሳዛኝ ሁኔታ በቡሩንዲና ብሩዋንዳ የሆነው ይህ ነው። ለዘመናት የቆዩ የአናሳው ጎሳ (ቱሲ) እገዛዞች ስልጣኑን ብቻ ሳይሆን ጥቅማጥቅሙን ሁሉ ለራሳቸው አድርገው ብዙሃኑን (ሁቱውን) እንደበታቻቸው ቆጥረው በመካከላቸው ጓደኝነትም ሆነ ጋብቻ እንዳይኖር ነውር እስኪሆን ህብረተሰቡን ቀየሩት። የማትቀረው ቀን ደርሳ ብዙሃኑ ስልጣን ላይ የወጣበት ግዜ ሁቱዎች ቱሲዎቹን ካገር በማሰደድና በመግደልም ተበቀሏቸው። በመካከላቸውም ባለው የከፋ ጥላቻ የተነሳ ሁል ግዜ በጥርጣሬ እየኖሩ ይገኛሉ።

የትግራይ ህዝብ ደግሞ እራሱን እንደአናሳ ማየት የለበትም። የዘር ፖለቲካ ማይኖሪቲ አደረገው እንጂ የብዙሃኑ እካል ነው። የትግራይ ገበሬ ፍላጎት ከትግራዩ ቢሊየነር ይልቅ ከወሎው ወይንም ከእርሲው ገበሬ ይመሳሰላል። የኢትዮጵያ ገበሬዎች ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙሃን ናቸው። ስለሆነም ህብረብሄር ድርጅቶች ውስጥ ሆኖ ቢታገል የመገለል እድሉን በትልቁ ይቀንሰዋል። ለዚህም የካናዳ ግዛት የኬቤክ ልምድ ጠቃሚ ነው። በካናዳ ፓርቲ ኬቤኳ የሚባል ብሄር ተኮር ፓርቲ፤ ፈረንሳይኛ ተናጋሪው የኬቤክ ግዛት ከሌሎቹ እንግሊዘኛ ተናጋሪ ግዛቶች እንዲገነጠል ብዙ ጥረት እድርጓል። የግዛቱን ስልጣንም ባሸነፈም አጋጣሚዎች ባይሳካለትም ሁለቴ (1980 እና 1995 እኤአ) ለመገንጠል የህዝብ ውሳኔ እድርጎ ነበር። በኬቤክ ግዛት የዚህ ፓርቲ እባላት እንዳሉም ግን የህብረ ብሄር ፓርቲዎች እባላት የሆኑ ብዙ ኬቤካውያኖች እሉ። እንዲያውም የኬቤክ ህዝብ የካናዳ 23% ብቻ ያህል ቢሆንም ባለፉት 50 ዓምታት 3 የካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ከኬቤክ የመጡ ናቸው። የስላጣን ዘመናቸውም በድምሩ 30 ሲሆን የእንግሊዘኛ ተናጋሪዎቹን ጠቅላይ ሚኒስትሮች ዘመን ድምርን ይበልጣል። እነርሱም የተመረጡት ህብረ ብሄር

ፓርቲዎችን ወክለው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ነው። ባንጻሩ ፓርቲ ኬቤኳ በምንም ተዓምር የካናዳን ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሊረከብ አይችልም። ምክንያቱም እራሱን እናሳው ኬቤኳ ብሄር ላይ ብቻ ወስኗልና።

ኢህአደግ ህብረብሄር ነውና እሱን መከተል እንቀጥላለን ትሉኝ ይሆናል። ሆኖም ሁላችንም እንደምናውቀው እስከ ቅርብ ድረስ የኢህአደግ ሞተር ህወሓት ነው። ሌሎቹ ለይስሙላ ናቸው። ከዚህ ውጭ እንደፓርቲ ሊቀጥል ይችላል የሚለው ነገር ያጠራጥራልና የትግራይም ህዝብ ባይተማመንበት ይሻላል። ሆኖም ኢህአደግ እራሱን ቢቀይርና እውነተኛ ህብረብሄርና ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ቢሆን እሰየው ነበር። በብቸኝነት አገሪቷን ሲመራ ያገኛቸውን አንዳንድ ልምዶች ለአገሪቷ ሊያበረክት ይችላልና።

ለማጠቃለልም ምናልባት ሰማይ ሊወድቅ ያህል መጪው ላስፈራቸው የህወሓት ደጋፊ ትግራውያን ማለት የምፈለገው፥ የሚከተለውን ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አንቅሮ አልተፋችሁም። ወደቀድሞው ፍቅሩ በቀላሉ ሊመለስ ይችላል። ሆኖም አሁንም ቢሆን ከብዙ ትግራውያን እንደምንሰማው ገሃዱን ሃቅ ብትክዱ ወይንም በሃይል ለውጡን ለመቀልበስ ብትሞክሩ ህዝቡን ወደበቀል ልትገፉት ትችላላችሁና እኩል የምንከባበርባትን ኢትዮጵያን እብረን እንገንባ። የህወሓት መንገድ እንደማያዋጣ አያችሁት። ይህንን እንቅፋት አብረን እንለፍና ሁላችንም ለተሻለች ኢትዮጵያ እንስራ፥ ስንከባበር መንገዱ ሁሉ ቀላል ይሆንልናል። ልጆቻችን መሰደዳቸው ይቀራል። ከጦርነት አዙሪት እንወጣልን። ያለጥፋታችን አንታሰርም፥ አንገደልም። እያንዳዱም የሚያፈራው ሀብት በተገቢ መንገድ ስለሚሆን ነገ ተቀማሁኝ ብሎ ሳይፈራ የተረጋጋ ህይውት ይኖራል። አለበለዚያ ግን ክፍፍላችን ለጠላቶቻችን መግቢያ በር ይሆንና ለኛ ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችንም ድህነትን፥ ርሃብን፥ ጦርነትን፥ስደትን እናወርሳለን።

መላው የኢጥዮጵያ ህዝብም የራሱን ቁስል ብቻ ማየት ይተው። አማራው ለትግሬው፥ ትግሬው ለኦሮሞው፤ ኦሮሞው ለወላይታው መብት ማሰብ ሲችል ፍቅር ይዳብራል። የሃውዜን መድብድብ የትግራውያን ሳይሆን የሁሉም ቁስል መሆን አለብት። የአርባጉጉ ስቃይ የአማራ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ጸጸት መሆን አለበት። ለሞያሌ ግድያ ኦሮሞ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ፍርድ ጠያቂ መሆን አለብት። ያኔ አንድ ትልቅ ኢትዮጵያን እንገነባለን።

ከፍቅር ይሻላል።